# የተከራይ
# ማኅልበቻ ጥቅል

ከ

**ዲስትሪክት ኦፍ ኮለምቢያ የሕግ እርዳታ ማህበር**
**(The Legal Aid Society of the District of Columbia)**



# የመሳሪያ ጥቅላችን ላይ እንኳን በደህና መጡ!

ይሄንን መመሪያ ያዘጋጀነው በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የሚገኙ ተከራዮች የቤት መብታቸውን እንዲያራምዱ የሚያስፈልጋቸውን ዕውቀት እና ኃይል ለመስጠት ነው። ይሄ መመሪያ ያግዙታል ብለን እናምናለን፦

- ሕጉን እና መብቶችዎን መረዳት፣
- የመኖሪያ ቤት ችግሮች ሲያጋጥሞት ምን ማድረግ እንደሚችሉ መረዳት፣
- ከእርስዎ ጎረቤቶች ጋር መደራጀት፣ እና
- ጠበቃ መቼ እንደሚያናግሩ ማወቅ።

ይሄ መመሪያ የተከራዮችን መብቶች እና የሕግ አማራጮች እስከ ሜይ 25 ቀን፣ 2021 ዓ.ም ድረስ ይገመግማል። ይሄንን መመሪያ በሚ ጠቀሙበት ሰዓት ሕጉ ተቀይሮ ሊሆን ይችላል። ስለ ሁኔታዎ ጥያቄዎች ያለዎት ከሆነ፣ ከጠበቃ ጋር መነጋገር አለብዎ።

ሌጋሌ ኤድ ለዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ነዋሪዎች ነፃ የሕግ አገልግሎቶች ይሰጣቸዋል። የቤት ክራይ ችግር ያለብዎ ከሆነ እና የሕግ ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ፣ በብዙ መንገዶች የሌጋል ኤድ አገልግሎቶች ላይ ማመልከት ይችላሉ።

- ኦንላይን ላይ ማመልከት ይችላሉ፦ https://www.legalaiddc.org/online-intake/
- በስልክ ማመልከት ይችላሉ፦ (202) 628-1161

በአካል በመገኘት ማመልከት ይችላሉ። እባክዎ በአካል ማመልከት ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት (202) 628-1161 ላይ ይደውሉ።

# መሰረታዊ ነገሮች

## በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የአከራይ-ተከራይ ሕግ

### በዲሲ ውስጥ፣ ለተወሰኑ ምክንያቶች ብቻ አንድ አከራይ ከቤት ሊያስወጣዎ ይችላል፣

እነዚህን ጨምሮ፦

- የቤት ክራይ መክፈል ላይ ከዘገዩ፣ ወይም
- በአሳሳቢ በሆነ ደረጃ የሊዝ ስምምነቱን ከጣሱ።

### አንድ አከራይ በሚከተሉት ምክንያቶች ከቤት ሊያስወጣዎት አይችልም፦

- የቤት ክራይዎ ውልዎ "ጊዜው ካለፈበት፣"
- አከራይዎ ያልወደድዎ ከሆነ፣
- ቤትዎ ላይ ጥገና የሚጠይቁ ከሆነ፣ ወይም
- አከራይዎ ቤቱን እየሸጠው ከሆነ።

### ከክራይ ቤት የማስወጣት ሂደት

ምንም እንኳን አከራዩ እርስዎን ከቤት ለማስለቀቅ ሕጋዊ መሰረት አለኝ ብለው ቢያምኑም፣ የመከላከያ ነጥቦች ሊኖሮት ይችላል። ምንም እንኳን መደበኛ ደብዳቤ ወይም ማስታወቂያ ቢያገኙም፣ መልቀቅ የለቦትም። ለመውጣት ከመወሰንዎ በፊት ጠበቃዎን ማነጋገር አለብዎ።

አከራይዎ ከቤት ሊያስወጣዎ የሚፈልግ ቢሆንም፣ ከዳኛው ፈቃድ ለማግኘት ወደ ፍርድ ቤት መሄድ የለባቸውም። የፍርድ ቤት ወረቀት ያገኙ ከሆነ፣ ስለ አማራጭዎ ለማውራት ጠበቃዎን ያግኙ። ያስታውሱ፣ አከራይዎ ጠበቃ ያለው ከሆነ፣ ያ ጠበቃ እርስዎን ለማገዝ አልተቀጠረም-- ጠበቃው የሚያግዘው ለአከራዩ ነው። የራስዎን ጠበቃ ለማግኘት ሁልጊዜ መሞከር አለብዎ።

አከራይዎ ወደ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ከቤት ሊያስወጣዎት የሚሞክር ከሆነ፣ ጠበቃ ያግኙ! ሕገወጥ ከቤት የማስወጣት እንቅስቃሴዎች ምሳሌዎች እነዚህን ናቸው፦

- መብራት ኋይል ማቋረጥ፣
- ውሃ ቧንቧ ማቋረጥ፣
- የበር ቁልፎችን መቀየር፣
- መንገዶች ላይ ንብረቶችዎን መወርወር፣ ወይም
- ኢሚግሬሽን እደውላለሁኝ ብሎ ማስፈራራት።

# የሁኔታዎች ችግሮች

## በቤቱ ውስጥ ስለሚገኙ ችግሮች ምን ማድረግ እችላለሁ?

### አስተማማኝ እና የጽዳት ሁኔታዎች ባሟላ መልኩ ቤቶቹን እንዲጠብቁ የዲሲ ሕግ ይጠይቃል።

አከራይ ማስተካከል ያለባቸው አንዳንድ የተለመዱ ችግሮች የሚያካትቱት፦

- አይጥ እና የበረሮ መራባት፣
- በትክክል የማይቆለፉ በሮች እና መስኮቶች፣
- የሚንጠባጠቡ ነገሮች፣
- ምንም ማሞቂያ ወይም ሙቅ ነገሮች።

### አከራዬ ጥገናዎች እያከናወነ ወይም የአይጦችን፣ አይጠመጎጦችን፣ እና በረሮዎችን ስርጭት እያቆመ አይደለም። ምን ለማድረግ እችላለሁኝ?

**1. ፎቶ እና ቪዲዮ ያንሱ።**

ይሄ ለአከራዩ ችግሩ በትክክል ምን እንደሆነ ለማሳየት ይጠቅማል። እነዚህ ድንገት አከራዩ ጥገናውን የማይፈጽም ከሆነ እንደ ማስረጃዎ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ኦንላይን ላይ ያስቀምጧቸው እና በምትክ ያስቀምጧቸው።

**2. ያነሷቸውን ፎቶዎች እና ቪዲዮዎች ለአከራዩ ይላኩለት እና አከራዩ ጥገናዎቹን እንዲፈጽም ይጠይቁ።**

የእርስዎን ጥሪ ካለማንሳት የተላከላቸውን ፎቶ ችላ ማለት ለአከራዮቹ ይከብዳቸዋል።

ስለ ችግሩ ለአከራዩ ለማሳወቅ የጹሁፍ መልዕክት፣ መደበኛ ደብዳቤ፣ ወይም የእጅ-ጽሁፍ ማስታወሻ ጥሩ መንገዶች ናቸው። የትኛውም ዓይነት ዘዴ ይምረጡ፣ የጽሁፍ መልዕክቱንበቅጂ መልክ በማስቀመጥ፣ ኢሜይሉን በማስቀመጥ፣ ደብዳቤውን ቅጂ በማድረግ፣ ከመላክዎ በፊት የማስታወሻውን ፎቶ ማንሳት አለብዎ።

በዚህ ጥቅል ላይ የናሙና ደብዳቤ እና ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ማመሳከሪያ አለ። ይሄንን እንደ ምሳሌ መጠቀም ይችላሉ፣ ወይም ሞልተውት ለአከራይዎ ቅጂውን መስጠት ይችላሉ።

# የሁኔታዎች ችግሮች
## የቀጠለ

**3. አከራይዎ ችግሩ ላይ ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ፣ DCRA ጋር ይደውሉ።**

DCRA (የሸማቾች እና የቁጥጥር ጉዳዮች መምሪያ (Department of Consumer and Regulatory Affairs)) ለመኖሪያ ቤት ሕግ ጥሰቶች ሕንፃዎች እና መኖሪያ ቤቶችን የሚመረምር የዲሲ መንግስት ኤጀንሲ ነው። DCRA ጥሰቱ የሚያጋጥመው ከሆነ፣ ለአከራይዎ ማሳወቅ እና ለአከራይዎ የተፃፈ ደብዳቤ መስጠት ይጠበቅባቸዋል። DCRA ለጥሰቱ የቤት አከራይዎ ቅጣት ሊቀጣ ይችላል። ነፃ ምርመራ እንዲደረግልዎ ለመጠየቅ (202) 442-9557 ላይ መደወል ይችላሉ።

የ DCRA መርማሪን ሪፖርት መጠየቅ እና ቅጂውን እንደያዙ ያረጋግጡ። አከራዩ አሁንም ቢሆንም ጥገናዎቹን የማያከናውን ከሆነ፣ ይሄ ቆይቶ ጠቃሚ ማስረጃ ሊሆን ይችላል።

**4. ያ ያልሰራ ከሆነ፣ የዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤቶች ጉዳዮች የሚታይበት ቀን ላይ ክስ መመስረት ይችላሉ።**

Tየዲሲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤቶች ሁናቴዎች ቀን (Housing Conditions Calendar) የሚባል ልዩ የፍርድ ቤት ክፍል አላቸው። የዚህ ፍርድ ቤት ክፍል የተዘጋጀው ጥገናዎችን ለማይፈጹሙ አከራዮችን ተከራዩች ለሕግ የሚያቀርቡበት ነው። እንደዚህ ዓይነት ክስ ከመመስረት ሊያገኙ የሚችሉት የመጨረሻው ነገር አከራዩ ጥገናዎች እንዲያደርግ ማስገደድ ነው - የቤቶች ሁኔታዎች ቀን ክስ ላይ ለጉዳት ካሣ አያገኙም።

የቤቶች ሁኔታዎች ቀን ክስ መመስረት ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ሌጋል ኤድን (202) 628-1161 ላይ ይደውሉ።

**5. ያ የማይሰራ ከሆነ፣ የቤት ክራይዎን አለመክፈል ይሞክሩ፣ ነገር ግን የሚመጣውን አደጋ ይወቁ።**

በዲሲ ውስጥ፣ አከራዩ የክራይ ቤቱን በአስተማማኝ፣ በንጹህ ሁኔታ፣ ወይም ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ ጥገናዎችን የማያከናውን ከሆነ ተከራዮች ሁሉንም ወይም ከፊሉን የቤት ክራይ ገንዘብ የመያዝ(ያለመክፈል) መብት አላቸው።

ሆኖም ግን፣ የቤት ክራይዎን ስላለመክፈልዎ ትክክል እንደሆነ እና እንዳልሆኑ መወሰን የሚችለው ዳኛ ብቻ ነው፣ እና አከራዩ አሁንም ቢሆን ሙሉውን ሆነ ከፊሉን የቤት ክራይ መጠን ካልከፈሉ ፍርድ ቤት ሊያቆሞት ይችላል።

# የሁኔታዎች ችግሮች
## የቀጠለ

በዚህም ምክንያት ነው ክራዩን መያዝ አደጋ ያለው፣ ምክንያቱም ፍርድ ቤት ሊከሰሱበት የሚችሉት ሁኔታ ላይ ራስዎን እያስቀመጡ ነው። ይሄ የእርስዎ ብድር ሁኔታ እና ለወደፊት ቤት ለመከራየት ሲያመለክቱ እና ተቀባይነት ማግኘትዎ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያመጣ ይችላል። የፍርድ ቤት ቀን ያመለጥዎ ከሆነ ወይም በክሱ የተሸነፉ ከሆነ፣ በተጨማሪም ከቤት እንዲወጡ ሊገደዱ ይችላሉ።

የእርስዎን ክራይ ገንዘብ መያዝ ላይ ብዙ አደጋዎች አሉ፣ ስለዚህ የቤት ክራይ ላለመክፈል ከመወሰንዎ በፊት ጠበቃ ሊያናግሩ ይገባል።

የቤት ክራይዎን ላለመክፈል የወሰኑ ከሆነ፣ ገንዘቡን ሊነኩት የማይችሉበት ቦታ (ልክ እንደ ቁጠባ ሒሳብ ደብተር) ውስጥ በአስተማማኝ ሁኔታ ለይተው ያስቀምጡት። የቤት ክራይ አለመክፈልዎ አግባብ አልነበረም ብሎ ዳኛ ከፈረደ፣ ከቤት ለመውጣት እንዳይገደዱ ያልከፈሉትን ሙሉ ወይም ከፊል ገንዘብ መክፈል ያስፈልጎታል።

የቤት ክራይዎን ላለመክፈል የወሰኑ ከሆነ፣ አከራዩ ጥገናዎችን ባለማከናወኑ ምክንያት የቤት ክራይ ገንዘቡን እንደያዙት የሚገልጽ ደብዳቤ ለአከራይዎ ደብዳቤ መፃፍ አለብዎ። በደብዳቤዎ ላይ፣ አከራዩ ምን ማድረግ እንዳልቻለ በግልጽ ያስቀምጡ። ለአከራይዎ ስለሁኔታዎቹ የሚገልጹ ፎቶዎች ያላኩላቸው ከሆነ፣ አሁን ያንን ያድርጉ።

### 6. ስለ ችግሮችዎ ለጎረቤቶችዎ ያነጋግሩ፣ እና የጋራ መፍትሔ እንዳለ ይመልክቱ።

ቁጥራቹህ በበዛ ቁጥር ኋይል ይኖራቹሃል። ቤትዎ ላይ አከራዩ ጥገናዎች የማያከናውን ከሆነ፣ የጎረቤቶችዎ ቤት ላይ ጭምር ጥገና እያከናወኑ እንዳልሆነ የሚሆንበት ዕድል ሰፊ ነው።

ጎረቤቶችዎን ማነጋገር በራስ መተማመንዎን የሚያሳድጉበት እና እንደ ተከራይ ያለዎትን መብት የሚያካፍሉበት ምርጡ መንገድ ነው። እርስዎ እና ጎረቤቶችዎ ተመሳሳይ ስትራቴጂ ለመከተል የወሰናቹህ ከሆነ (ልክ እንደ DCRA ጋር መደወል፣ የቤቶች ሁናቴዎች ቀን ፍርድ ቤት ላይ ክስ መመስረት፣ ወይም ሁላቹህም የቤት ክራይ ባትከፍሉ)፣ ከአንድ ሰው ድርጊት ይልቅ የእናንተ የጋራ እርምጃዎች ከፍተኛ ሊሆን ይችላል።

**ያስታውሱ፣ የህግ ድጋፍ ማግኘት የምትፈልጉ ከሆነ፣ ሌጋል ኤድን (202) 628-1161 ላይ መደወል ይችላሉ።**

# ከብዛት ጥንካሬ
## ከጎረቤቶችዎ መደራጀት

### ከጎረቤቶቼ ጋር ለምን እደራጃለሁኝ?

ጥገናው እንዲከናወን ይፈልጋሉ፣ ነገር ግን አከራይዎ የእርስዎን ጥያቄዎች ችላ ይላል? ከአስተዳደር ኩባንያዎ የማስፈራሪያ ደብዳቤዎች ደርሶታል? ስለ ቤትዎ አስተማማኝነት እና ምቾት ሌሎች ስጋቶች አሉት?

ብቻዎትን አይደሉም። ጎረቤቶችዎ ተመሳሳይ ችግሮች ሊያጋጥማቸው ይችላል።

እርምጃዎችን ለመውሰድ የአከራዮችን ቡድን ማደራጀት

- የቤት አከራይዎ የተከራዮችን ፍላጎቶችን እንዲያሟላ ያስገድዱት፣ ምንም እንኳን አከራዩ ለአንድ ተከራይ ምላሽ ባይሰጥም።
- ሁሉንም ነገር ለብቻ የማድረግ ዕዳ በመቀነስ ለተከራዮች መብቶቻቸውን እንዲያራምዱ ያግዛቸዋል።
- ሕንፃዎ ላይ ችግሮችን በፍጥነት እና በጋራ ለመፍታት መዋቅር ይፍጠሩ እና ጥያቄዎችዎ ላይ ላይ አከራዩ ይበልጥ ምላሽ ሰጪ እንዲሆን ያድርጉት።

### የተከራዮች ሕብረት ምንድን ነው?

የተከራዮች ሕብረት ችግሮችን ለመፍታት እና በቡድኑ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ተገናኝተው ችግሮች ላይ ውይይት የሚያደርጉ ተመሳሳይ ሕንፃ ላይ የሚኖሩ ተከራዮች ናቸው።

የተከራዮች ማህበር በሕግ መንገድ መቋቋም አያስፈልጋቸውም። መደበኛ፣ በሕግ የተዋቀረ የተከራዮች ማህበር ልክ እንደ የፍርድ ቤት ክስ መመስረት ዓይነት፣ ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ ሊችሉ ይችላሉ። የተከራይ ማህበርዎ፣ ሆኖም ግን፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ወሳኝ ድምጽ ለመሆን መንግስት ጋር በሕግ መዋቀር ወይም መመዝገብ አያስፈልገውም። በህግ ያልተዋቀሩ በጣም ብዙ ስኬታማ የተከራይ ቡድኖች አሉ!

# ከብዛት ጥንካሬ
## የቀጠለ

### የተከራዮች ሕብረት ምን ያደርጋል?

የተከራይ ማህበር ዓባላቱ የሚፈልጉት ማንኛውም ነገር ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይችላል። አከራይዎ ሕንፃውን ለመሸጥ የሚፈልግ ከሆነ፣ የክራይ ሕንፃዎች ሽያጭ በተመለከተ መብታቸውን ለማስከበር ተከራዮች ሊደራጁ ይችላሉ። ከመላው ሕንፃ ጋር የሚገናኙ ችግሮች ያሉ ከሆነ፣ ተከራዮች ጥገና እንዲከናወን ሊደራጁ ይችላሉ። የተከራዮች ሕብረት ለእርስዎ እና ለጎረቤቶችዎ የጋራ ግቦች ለመለየት እና እንዴት እንደሚያሳኳቸው ስትራቴጂ የማውጣት ዕድል ይፈጥራሉ።

### ሕንፃዎች “የክራይ አድማ” አደረጉ ሲባል ሰምቼአለሁኝ። ምን ማለት ነው?

የክራይ አድማ ማለት በሕንፃ ውስጥ የሚኖሩ ተከራዮች በመተባበር ለአከራዩ የቤት ክራይ ክፍያውንሲይዙ (ላለመክፈል ሲወስኑ) ነው። የክራይ አድማ አከራይ ጥገናዎች እንዲያከናውን ወይም ሌሎች እርምጃዎችን እንዲወስድ ያስችሉታል። በአብዛኛው፣ ልምድ ባላቸው፣ የባለሙያ አደራጆች በመጠቀም የክራይ አድማ በተከራይ ሕብረቶች ይደረጋሉ።

ውጤታማ የክራይ አድማ የሚያስፈልጉት፦

- ዕቅድ ማውጣት እና ትብብር። ተከራዮች ልክ እንደ ኢስክሮው የባንክ አካወንት ዓይነት፣ አስተማማኝ ቦታ ላይ የክራይ ገንዘባቸውን እንዴት እንደሚያስቀምጡ መወሰን አለባቸው። በተጨማሪም አከራዮች አድማውን መቼ እንደሚያቆሙ መወሰን አለባቸው።
- ሊመጡ የሚችሉ አደጋዎችን መረዳት። ተከራዮች ክራይ የማይከፍሉ ከሆነ፣ አከራዩ ተከራዮችን ወደ ፍርድ ቤት ሊወስድ ይችላል፣ እና ለአንድ ሰው ብድር መውሰድ እና ለወደፊቱ ቤት መከራየት ላይ መጥፎ ሊሆን ይችላል። የፍርድ ቤት ቀን ያመለጥዎ ከሆነ ወይም በክሱ የተሸነፉ ከሆነ፣ ከቤት እንዲወጡ ሊገደዱ ይችላሉ።

በእነዚህ አደጋዎች የተነሳ፣ የክራይ አድማ ከመጀመራቹህ በፊት ጠበቃ እና ልምድ ያላቸው የተከራይ አደራጆችን እንዲያነጋግሩ እንመክሮታለን። እባክዎ የክራይ አድማ ለማድረግ ማደራጀት ወይም የቤት ክራይ ገንዘቡን መያዝ የሚፈልጉ ከሆነ ቢሮአችን ላይ ይደውሉ እና ከእነዚህ ቡድኖች ከአንዳቸው ጋር ይገናኙ፦

- የቤቶች ማማከር አገልግሎቶች (Housing Counseling Services:)፦ በ (202) 900-9464
- ላይ ይደውሉ።
- የላቲኖ የኢኮኖሚ ልማት ማዕከል(Latino Economic Development Center:)፦ (202) 540-7439 ላይ ይደውሉ።

# ከብዛት ጥንካሬ
## የቀጠለ

## የተከራይ ሕብረት እንዴት መፍጠር እችላለሁኝ?

### 1. ችግሩን ይለዩ?

ተከራዮች በተለያዩ ብዙ ችግሮች ምክንያት ሊደራጁ ይችላሉ። በቤትዎ ላይ ሁኔታዎች፣ ችግሮች እና የቤቶች ሕግ ጥሰቶች አሉ? ከአከራይዎ የማስፈራሪያ ደብዳቤ ደርሶታል? የሕንፃዎ የጋራ ቦታዎች ላይ ችግሮች አሉ?

### 2. የእርስዎን ጎረቤቶች ያነጋግሩ።

ጎረቤቶችዎ ተመሳሳይ ችግር ገጥሟቸው ከሆነ ይጠይቋቸው።የማያቋቸው ወይም ብዙ የማይግባቧቸው ጎረቤቶች ያሉ ከሆኑ፣ በራቸው ላይ ያንኳኩ ወይም አከራዩ የሚሰራውን ስራ በተመለከተ ያላቸን ሐሳብ በማስታወሻ ይጠይቁ። የእርስዎን ችግር መጀመሪያ ላይ ማጋራት ሌሎች ሰዎች የእነሱ ለማጋራት ይቀላቸዋል።

በሕዝብ የጤና ድንገተኛ ጊዜ ላይ፣ በር ማንኳኳት እና በአካል መገናኘት ለእያንዳንዱ ግለሰብ አስተማማኝ አማራጭ ላይሆን ይችላል። ከዚያ ይልቅ፣ ስልክ ቁጥርዎን በመጠቀም በራሪ ጽሑፎችን መለጠፍ (የራስዎን ቁጥር ለመጠቀም የማይፈልጉ ከሆነ Google voice ይጠቀሙ) ወይም WhatsApp ወይም ተመሳሳይ መተግበሪያ የቡድን ውይይት መተግበሪያ ይጠቀሙ። በ Zoom፣ Google Meet፣ ወይም በሌላ በየነገጽ።

### 3. ስብሰባዎችን በመርሀግብር ያስይዙ እና ሁሉንም ሰው ይጋብዙ።

ጉዳዩ እንዲዳረስ በራሪ ጽሑፎችን ይለጥፉ። በታቻለ መጠን ብዙ ጎረቤቶችን እንደሚመጡ ለማድረግ ይሞክሩ ስለዚህ ሁሉም ድምጾች እንዲሰሙ ያድርጉ። ለሰዎች የስብሰባው ርእስ ምን እንደሆነ ይንገሯቸው፣ በዚህም መሰረት ምን እንደሚጠብቁ ያውቃሉ።

ስለ ተከራዮች መብቶች ጥያቄዎች ያለዎት ከሆነ፣ ይደውሉልን። ለእርስዎ እና ለሌሎች ተከራዮች “መብቶችዎን ይወቁ” የሚያስተምሩ ቡድኖችን ልናገኝ እንችላለን።

# ከብዛት ጥንካሬ
## የቀጠለ

**4. ስብሰባው ላይ፣ ተወያዩ፣ አዳምጡ፣ ግቦች አስቀምጡ፣ እና ማስታወሻዎችን ይያዙ።**

- ማን እንደተሳተፈ እና እያንዳንዱን ሰው እንዴት እንደሚያገኙ ማወቅ እንዲችሉ ለስብሰባው የመፈረሚያ ሰነድ ያዘጋጁ (ወይም የቪዲዮ ጥሪ የሚያደርጉ እንደሆነ ማን እንደተሳተፈ ማስታወሻ ይያዙ)።
- እርስዎ እና ጎረቤቶችዎ ያጋጠማቹህ የጋራ ችግሮችን ይለዩ። የእርስዎ አከራይ የሚያስፈልጉትን እርምጃዎች እንዲወስድ መፍትሔ ሰንዝሩ። የሚፈልጓቸውን ነገሮች ዝርዝር በደብዳቤ መፃፍ እና ብዙ ተከራዮች እንዲፈርሙበት ማድረግ የተሻለ ሊሆን ይችላል?እርስዎ እና ጎረቤቶችዎ በሕንፃ ውስጥ እንዲሻሻሉ የሚፈልጓቸው ነገሮች አሉ? ይናገሩ፣ ያዳምጡ እና ግቦችን ለማስቀመጥ በጋራ ይስሩ እና የቡድኖን ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ይለዩ።

- ምን እንደተባለ ለማስታወስ እና መሳተፍ የማይችሉ ሰዎች ምን እንደተደረገ ማወቅ እንዲችሉ ማስታወሻ ይያዙ።

**5. ወደ ሚቀጥለው ደረጃ ያሸጋግሩት።**

የተከራይ ሕብረቱን በሕግ እንዲቋቋም ያድርጉት። በሕንፃዎ ላይ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ አንዴ በጋራ መስራት ሲጀምሩ፣ የእያንዳንዱ ሰው ድምጽ መሰማቱን ለማረጋገጥ ስብሰባ እንዴት እንደሚካሄድ መሰረታዊ የአገባብ ሕጎችን ማስቀመጥ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች የተወሰኑ ግቦች ወይም ተግባራት ላይ እንዲሰሩ ማድረግ፣ እና ግልጽ የሆነ የዓባልነት መስፈርት መፍጠር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

**6. በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ግብዓቶች ጋር ይገናኙ።**

ፐየእናንተን የተከራይ ሕብረት ሊያግዙ የሚችሉ ብዙ የባለሙያ ድርጅቶች አሉ። እነዚህ ድርጅቶች፣ የጋራ ሕ
መፃፍ ላይ ማገዝ፣ ወይም ሕጋዊ ቦርድ መፍጠር ላይ ስልጠና ሊሰጡ ይችላሉ። መሪዎችን መምረጥ ወይ
መስረታዊ ሕጎችን ማስቀመጥ ላይ እገዛ የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ ከእነዚህ ድርጅቶች አንዱ ላይ ይደውሉ፦

- የቤቶች ማማከር አገልግሎቶች (Housing Counseling Services:)፦ በ (202)
- 900-9464 ላይ ይደውሉ።
- የላቲኖ የኢኮኖሚ ልማት ማዕከል(Latino Economic Development Center:)፦ (202) 540-
7439 ላይ ይደውሉ።

# ከብዛት ጥንካሬ
የቀጠለ

## የእኛ የተከራይ ሕብረት ስኬትማ እንዲሆን እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁኝ?

የጋራ ግቦችን መለየት እና ከጎረቤቶችዎ ጋር ሕብረት ፈጥሮ መቆየት ብዙ ስራ ይጠይቃል። ከግምት ሊያስገቧቸው የሚችሏቸው ጥቂት ጥቆማዎች በመቀጠል ተቀምጠዋል፦

- በመላው ሕንፃ ላይ የሚገኙ ችግሮች ላይ ያተኩሩ። ልዩነቶች ቢፈጠሩም፣ ሊከፋፍሏቹህ እንደማይገባ፣ ይቀበሉ። አከራዮች ወይም አስተዳደሮቹ ሕብረታቹህን ለማዳከም በእርስዎ እና በጎረቤቶችዎ መካከል ማንኛውም ዓይነት ክፍፍሎች ወይም ልዩነቶችን ለመፍጠር ሊሞክሩ ይችላሉ።

- እያንዳንዱ ድምጽ መሰማቱን በማረጋገጥ ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚያስችሉ ሕጎችን ያስቀምጡ። ከስብሰባው በፊት አጀንዳ እንዲያዝሎት ሊፈልጉ ይችላሉ፣ ተራ በተራ ተነጋገሩ፣ ውሳኔዎችን በድምጽ ብልጫ ያድርጉ፣ ወይም ሕብረቱን በመወከል ስልጣን ያላቸው ሰዎችን ወይም ቦርዶችን ይምረጡ። እነዚህን ሕጎች በጽሁፍ ማስቀመጥ ለመከተል እና እንዳይረሱ ለማድረግ ያግዛል።

## ያስታውሱ፣ አከራይዎ ተከራዮችን ሲደራጁ ጣልቃ መግባት ወይም ማቆም መሞከር በሕግ አይፈቀድለትም ።

አከራይዎ የሚከተሉትን ማድረግ አይችልም፦

- ከማህበረሰቡ መገናኛ ቦታዎች እንዳይገቡ ሊቆልፍብዎ ወይም የጋራ መገናኛ ቦታዎች ላይ መሰብሰብ እንደማትችሉ ሊነግራቹህ አይችልም፣
- በር ማንኳኳት እንዲያቆሙ ለመንገር፣ ወይም
- በራሪ ጽሁፎችን መገንጠል ወይም እንዳትለጥፉ መከለከል።

አከራይዎ የተከራይ ሕብረት ላይ ጣልቃ የሚገባ ከሆነ፣ እንዲያቆም ይንገሩት። ጣልቃ መግባታቸውን የሚቀጥሉ ከሆነ፣ የተነጋገሩበትን፣ ስልክ ጥሪዎች፣ ኢሜይሎች፣ ጹሁፎች፣ ፎቶዎች፣ ወይም ቪዲዮዎች እንደ ማስረጃ ያስቀምጡ፣ እና የባለሙያ ድርጅቶችን ያግኙ። እዚህ ላይ ሊያግዙ የሚችሉ ሁለት ድርጅቶች አሉ፦

- 
- የቤቶች ማማከር አገልግሎቶች (Housing Counseling Services:)፦ በ (202) 900-9464 ላይ ይደውሉ።
- የላቲኖ የኢኮኖሚ ልማት ማዕከል(Latino Economic Development Center:)፦ (202) 540-7439 ላይ ይደውሉ።

# የቤቶች ሕግ ጥሰት ደብዳቤ

አከራይ፦
አድራሻ
Washington, DC ZIP

ቀን

ውድ አከራይ፦

እኔ በዚህ አድራሻ ላይ የቤት ተከራይ ነኝ። በመኖሪያ ቤቴ ውስጥ ብዙ ችግሮች አሉ፣ እና እነዚህ ችግሮች ደግሞ የዲሲ ቤቶች ሕግ የጣሱ ናቸው። የእነዚህን ችግሮች ዝርዝር ለእርስዎ እየሰጠሁኝ ነው። በተጨማሪም ችግሮቹን ለማሳየት የተነሱትን ፎቶዎች እየሰጠሁኝ ነው።

እባክዎ ቤቴን ለመመርመር የምንገናኝበት ጊዜ ለመወሰን በስልክ/በኢሜይል ያግኙኝ እና እነዚህ ጥገናዎች መከናዎናቸውን ያረጋግጡ።

ተከራይ

ከአክብሮት ጋር፣

ተከራይ
አድራሻ
Washington, DC ZIP

# የቤት ችግሮች ማመሳከሪያ ዝርዝር

ቀን፡-፡ ____________________

## ማሞቂያ

[ ] አይበራም አይጠፋም (አንዱ ላይ ያክቡ) [ ] በቂ አይደለም

[ ] የማሞቂያው ግማሽ ክፍሎች የሉም/ተበላሽተዋል (ያብራሩ) ____________________

[ ] የአየር መቆጣጠሪያዎቹ ላይ ችግር አለ (ያብራሩ) ____________________

[ ] ሌሎች፡-: ____________________

## የአየር ማቀዝቀዣ/የአየር መቆጣጠሪያ

[ ] አይበራም አይጠፋም (አንዱ ላይ ያክቡ) [ ] ] በቂ አይደለም

[ ] የኤሲው ግማሽ ክፍሎች የሉም/ተበላሽተዋል (ያብራሩ)____________________

[ ] የአየር መቆጣጠሪያዎቹ ላይ ችግር አለ (ያብራሩ) ____________________

[ ] ሌሎች፡-____________________

## ኤሌክትሪሲቲ

[ ] ይጠፋል [ ] አደገኛ ነው (ያብራሩ) ____________________

[ ] አይበራም (የሚከተሉት ክፍሎች ላይ) ________________________________

[ ] የተሰበሩ መሰኪያዎች (የሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ) ________________________________

[ ]ሌሎች፡- ____________________

## ቧንቧ

[ ] ዝቅተኛ የውሃ ግፊት [ ] የሚንጠባጠብ ቧንቧ(ዎች)

[ ] ሽንት ቤቱ(ቶች) ውሃው መፍሰስ የማያቋርጥ [ ] የተደፈነ መታተቢያ/ገንዳ/ሽንት ቤት (ያክብቡት(ባቸው))

[ ] ሙቁ ውሃ የለውም [ ] የተደፈነ መታተቢያ/ገንዳ/ሽንት ቤት (ያክብቡት(ባቸው))

[ ] ሌሎች፦ ___________________________

## አነስተኛ እንስሳዎች

[ ] አይጦች/መጎጦች/የአይጥ ዘሮች (አንዱ ላይ ያክቡ(ቧቸው)) [ ] በረሮዎች

[ ] የአልጋ ቱሃኖች [ ] ሌሎች: ___________________________

## የውሃ ጉዳት/ሽጋታ

[ ] የውሃ ጉዳት/ምልክቶች (የሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ)፦ ___________________________

[ ] ሽጋት/አረንጓዴ መሆን [ ] ንቁ የውሃ ማንጠባጠብ(ቦች) (ያብራሩ)፦ ___________________________

[ ] ሌሎች፦ ___________________________

## መስኮቶች

[ ] በትክክል አይዘጉም/አይከፈቱም [ ] አየር/ነፋስ ያስገባሉ

[ ] ቀዳዳ/ክፍተቶች አሏቸው

[ ] የተቀደደ/የተነቀለ የመስኮት መከለያ አላቸው (የሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ)፦__________________

[ ] ሌሎች፦ ___________________________

## ግድግዳዎች/ጣሪያ

[ ] ] የተሰነጠቀ፣ ያበጠ፣ የተላላጠ ቀለም (በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ የትኛው(ዎቹ) እንደሆነ(ኑ) ያክቡ):

______________________________________________

[ ] የተሰነጠቀ፣ ያበጠ፣ የተላላጠ ቀለም (በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ የትኛው(ዎቹ) እንደሆነ(ኑ) ያክቡ):

______________________________________________

[ ] የወረደ ኮርኒስ (የሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ)፦ ______________________

[ ] ኮርኒስ ላይ ማንጠባጠብ (የሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ)፦ ______________________

[ ] ኮርኒስ ተከፍቷል (የሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ)፦ ______________________

[ ] ሌሎች፦ ______________________

## በሮች

[ ] የተነቀሉ/የተበላሹ/የማይሰሩ ዕቃዎች (ያክቡ (ቧቸው))

[ ] የተገነጠሉ መታጠፊያዎች/ዱካዎች

[ ] ] በትክክል አይከፈትም/አይዘጋም (በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ የትኛው(ዎቹ) እንደሆነ(ኑ) ያክቡ):

______________________________________________

[ ] በሚገባ አይቆለፍም (የሚከተሉት ክፍሎች ላይ)፦

______________________________________________

[ ] ] የፊት/የጀርባ በር ውሃ የሚያስገባ ነው (ብርሃን እና አየር የሚያስገቡ ክፍተቶች አሉት)

[ ] ሌሎች፦ ______________________

## ወለል

[ ] የተነቀሉ/የተሰበሩ/የተፈነቀሉ ወለሎች (ያክቡበት(ቧቸው))

[ ] ወለሎች በውሃ የተጎዱ ናቸው  [ ] ቀዳዳዎች/ክፍተቶች አሏቸው  [ ] የተነቀሉ/የተሰበሩ መለኪያዎች

[ ] የታችኛው ሲምንቶ ተጋልጧል  [ ] ምንጣፉ መቀየር ያስፈልገዋል

[ ] ሌሎች፦ ________________________

## የቤት ዕቃዎች

የሚከተሉት የቤት ዕቃዎች አይሰሩም/ተበላሽተዋል፦

[ ] ማቀዝቀዣው  [ ] የበረዶ ቤቱ  [ ] የስቶቭ ላይኛው ምድጃዎች  [ ] የወጥቤት ገንዳ/ቧንቧ

[ ] የምድጃው አየር ማውጫ  [ ] አቨኑ  [ ] ማይክሮዌቭ  [ ] የሳህን ማጠቢያ

[ ] ልብስ ማጠቢያው (የአንድ ቤት/የመላው ሕንፃ)  [ ] ማድረቂያው (የአንድ ቤት/የመላው ሕንፃ)

## ውጪ/መላው ሕንፃ

[ ] መግቢያ በር ተበላሽቷል  [ ] መግቢያ በር አይቆለፍም  [ ] የማይሰራ ሊፍት

[ ] ] በሩ ላይ የጎደሉ ነገሮች/ የበሩ መገጣጠሚያ የተነቀለ  [ ] የተገነጠለ/የማይሰራ የበር እጀታ

[ ] መግቢያ በሩ የበሩ ማቀፊያ ጋር አይገጥምም  [ ] የጎደሉ/የተሰበሩ ደረጃዎች/መወጣጫዎች

[ ] የጎደሉ/የተሰበሩ የጣራ ወለሎች  [ ] በውሃ የተጎዳ/የሚያፈስ ጣሪያ (ያብራሩ)_______________

[ ]  የተጋለጠ የኤሌትሪክ ሽቦ  [ ]ደብዳቤ ሳጥን ላይ ችግር (ያብራሩ) _______________

[ ] ሌላ፦ ________________________